# ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት (ሞወዐድ)
# Moresh Wegenie Amara Organization (MWAO)

Website: www.moreshwegenie.org E-mail: InfoAndPR@moreshweg

ትግላችን ትውልድ ተሻጋሪ ነው። የዐማራው መደራጀት የኅልውናው እና የማንነቱ መሠረት ነው።
Our struggle is trans-generation. Amara's organization is the basis of its existence and identity.

*ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት* *ቅዳሜ፣ የካቲት 21፣ ፪ሺ ፲፫ ዓ.ም. (Feb. 28, 2021)* *ቅጽ ፫ ቁጥር ፪*


# የኢትዮጵያ መዳኛ ዐማራው ከሌሎች አገር ወዳድ ወገኖቹ ጋር በመሆን መደራጀቱና ጠንካራ ኃይል ሆኖ መውጣት ብቻ ነው።

**"ለኢትዮጵያ እንደሀገር መቀጠል" በሚል ባዶ ድለላ በወልቃይት፣ ጠገዴ፣ ጠልምትና እራያ በመስዋእትነቱ ያስከበረውን ህልውናውንና ማንነቱን ለመቀማት የሚደረገው የኦሮሚማ ተረኞች ጥረት፣ በግልጽ ከነገሩን "በማሳመን ወይም ግራ ማጋባት" ስልታቸው የተለየ ስላልሆነ ዐማራውን መፈታተናቸው የማይቀረውን ውድቀታቸውን እንደሚያፈጥነው ሊያውቁት ይገባል። የፍትህ፣ የደህንነት፣ የመከላከያ፣ የምርጫና ሌሎች ተቋሞችን በተረኞች መሞላት የሚያሳየው አብይ አህመድ የሚመሩት የብልጽግ ን ፓርቲ አገዛዝ የወያኔ እሳቤንና አፓርታይድ ሥራዓት አስቀጣይ እንደሆነ አረጋግጧል። በተለይም በአማራው ህልውና ላይ ተረማምደው ስግብግብና አረመኔያዊ ህልማቸውን እውን ለማድረግ መሞከር ከታሪክና በቅርብ ካየነው የትግራይ ወያኔ ውድቀት አለመማር ነው።**

ኢትዮጵያ ባለፈቻቸው የማህበራዊ ዕድገትም ይሁን በአዝጋሚው የታሪክ ሂደት ውስጥ ራስን ከሌሎች ወገኖቹ ለይቶ የማያውቀው የዐማራ ሕዝብ ላለፉት 30 ዓመታት ያህል በጎጠኞች ከፋፋይ ፖለቲክ ምክንያት ለመከራ ተዳርጓል። አገራችን በዘር እሳቤ ብቻ የተመነዛዘረች እንድትሆን በሚደረገው ዘመቻ የዐማራው ህልውና ለአደጋ ተጋልጧል። በዚህም ምክንያት ላለፉት 30 ዓመታት በስልጣን ላይ የተፈራረቁት ሁሉ ዐማራው የሕግ ከለላ እንዳይኖረው በሚያደርጉት የዘረኝነት ፓሊሲ ምክንያት ብዙ ሚሊዮን ዐማሮች በግፍ እንዲሰዉ ተድርጓል።

በኢትዮጵያ ውስጥ የሕዝብ ልዕልና እንዲጎለብት፣ የዜጎች መሰረታዊ መብቶች እንዲከበሩ፣ ብሎም ህዝባዊ እውቅና ባለው መንግስት መመራት የአገሪቷን አንድነት የማስጠበቂያ መሰረት ነው ብሎ የሚያምነው ዐማራ እየተገደለና እየተሳደደ ነው። መንግስትም በአጥፊዎች ላይ አስፈላጊውን እርምጃ ሊወሰድ ባለመቻሉ የዐማራው እልቂትና ከባድ የሕይወትና የንብረት መስዋእትነቱ እጅግ የከፋ ሆኗል። በዛሬይቷ ኢትዮጵያ የጠቅላይ ሚንስትር ዐብይ መንግስት ለሚፈጸሙ ጸረ ዐማራ ኢሰብአዊ ድርጊቶችንና ወንጀሎችን አበረታች ለመሆኑ በግልጽ እየታየ ነው። የመንግስት ተብየው ተወካይዎችም ሁሉ ሳይቀሩ የዘር ማጥፋትና የዘር ማጽዳት ጥሪ እያስደመጡ ነው። በመሆኑም የዐማራ ብሔርተኝነት የትግል ስልት ለዘርፈ ብዙ ተግዳሮቶቹ ዋሳኝነቱ ገሃድ ሆኗል። ለዐማራ ሕዝብ ሁለንተናዊ ለውጥ የህልውናው ማረጋገጫና የሚደርስበትን ዘርፈ ብዙ ተግዳሮቶች መቀልበስ የሚችለው ለራሱ መድህን ራሱ ሐላፊነቱን አንግቦ በነቃ፣ በተደራጀ እና በታጠቀ ኃይል መመከት ሲችል ብቻ ነው።

በሰሞኑ **የኦነግ ዘረኞችና አጋሮቻቸው ባደረጉት ሰልፍ ላይ የተንጸባረቀውን ዐማራን እናጥፋ ጥሪ የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚ/ር ዐብይ በፌስቡካቸው ላይ ለጥፈውት ነበር። የለውጥ መሪ የተባሉት ጠቅላይ ሚኒስቴር የእልቂት ጠሪ መሪ ለመባል በቅተዋል። ከዚህም ጋር በተያያዥነት** በሰላማዊ መንገድ ብቻ የሚታገሉትን "ባልደራስና አብን የኢትዮጵያ ሕዝብ ጠላቶች ናቸው።" ብለው ሲያስተጋቡ ጉዳዩ በቀጥታ ዐማራን እናጥፋ የሚል እንድምታ ያለው ነው። በአገራችን የለውጥ መሪ መጥቷል ሲባል ተስፋ የተጣለባቸው መሪ፣ በአሁኑ ጊዜ የእልቂት ጠሪ መሪ ሆነው ተቀምጠዋል። ትህነግ ወያኔ ኮትኩቶ ያሳደጋቸው ጠቅላይ ሚንስትር፤ ዛሬም የሟቹን የመለሰን ራዕይ አንግበው ይራመዳሉ። በስልጣን ድልድልና በሐላፊነት ቦታዎችም ዐማራውን በማግለል ስልጣናቸውን እያስከበሩ በመሆኑ የሰሞኑ የእልቂት ጥሪ አዝማች መሆናቸው ሊያስደንቀን አይገባም።

የእኩይ ቡድኖችና የጥላቻ ስካር የጥፋት ተልእኮ ድንበሩን ካለፈ ብዙ ዘመን አስቆጥሯል። የኢትዮጵያን ችግር ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ይፈታሉ ያልናቸው ጠቅላይ ሚንስትር አብይ "የኦሮሞን ጥያቄ ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ እየሰራነው ነው" ሲሉ የትኛውን ጥያቄ እንዴት ይፈቱታል ብለን መጠየቅ ግድ ይለናል።

በኢትዮጵያ ለውጥ መጥቷል ከተባለበት ወቅት አንስቶ፣ የነሽመልስ አብዲሳን አዲስ አበባ ላይ "የነፍጠኛውን አከርካሪ ሰበርን" የሚሉትንና የቁማሩን አተገባበር ንንግር ሁሉ ብንተወው፣ የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚንስትር ዐብይ በአደባባይ የተናገሯቸውን ፀረ ዐማራ፣ ኢትዮጵያና አንድነት ንግግሮች ብንጠቅስና በተግባር እመሬት ላይ የሚፈፅሙትን ብናስተውል፣

· ጠቅላይ ሚንስትሩ በመሩት የፓለቲካ ፓርቲዎች ዉይይት ላይ የአብኑ አቶ ክርስቲያን ታደለ ህገመንግስቱ እንዲቀየር ጥያቄ ሲያቀርብ "ሕገ መንግስቱ ለአንድ ክልል ሲባል አይለወጥም" በማለት ዐማራው የሕግ ከለላ እንዳጣ እንዲኖር፣ ማንም በዐማራ ላይ የፈለገውን እንዲያደርግ ፈቅደዋል፣

· የአዲስ አባባን ህዝብ የሚወክል ከንቲባ ያስፈልጋል ለሚለው ጥያቄ ጠቅላይ ሚንስትሩ በሸራተን ሆቴል በስሜት ተሞልተው "ባለአደራ የሚባል ጨዋታ የምትጫወት ከሆነ ግልፅ የሆነ ጦርነት ውስጥ እንገባለን" በማለት አዲስ አበቤውን በሙሉ መብቱን ገፈው አስፈራርተው ነበር። የእነ እስክንድር ነጋም እስር የዚሁ ውጤት እንደሆነ እናምናለን።

· የኦሮሞ ልዩ ሃይል በብዙ መቶ ሺህ ሲደራጅና ሲመረቅ፣ በዐማራው ክልል ግን ያለውን አደረጃጀት ደሴ ላይ ህዝብ በተሰበሰበበት አዳራሽ በመወንጀል ልዩ ኃይሉ እንዲዳከምና እንዲፈርስም ሰርተዋል።

· ባገለገሉት የዘረኛ ሥርአት የምትታመስ ሀገር ውስጥ እያለን ስለዐማራው የህልውና ጥያቄና በወረራ ስለተያዙት የዐማራ ማንነቶች ሲጠየቁ፣ የዐማራ ብሔርተኝነት አደገኛ ነው የሚል መልስ ሰጥተዋል።

· በአዲስ አበባ ነባሩን ሕዝብ መንጥረው ከተማውን የአንድ ብቸኛ ነገድ አንጡራ ሃብት ባለቤት ለማድረግ በተያዘ ፕሮግራም ውስጥ በሴራው ተሳታፊ እንዲሆኑ በሚሰጧቸው ሹመትና መመሪያ አሳውቀዋል። በህሊና እስረኞቹ በእነእስክንድር ነጋ ላይም የሚሰራው ደባ ከዚሁ አላማ ጋር ተያያዥነት አለው።

· በባሌ ባሰሙት ዲስኩር ኦሮሞ ዝሆን ነው - ዘመኑ የእኛ ስለሆነ፣ እንሰብራለን፣ እንበላለን፣ እንጨፈልቃለን፣ እንገላለን ብለዋል።

· በአሜሪካ ጉብኝታቸው በዐማራው ላይ የዘር ማጥፋት ወንጀል አልተፈጸመም በማለት የቀደመውን ዘመን የትህነግ/ወያኔን ወንጀል ከደዋል ወይም ተከላክለዋል፣

· የኤርትራ ጦር በፍፁም ትግራይ ላይ ወያኔን ለማስወገድ ስንል አላስገባንም ካሉ በኋላ ዛሬ እንደሚሰማው የኤርትራ ጦር ሰላማዊውን የትግራይ ህዝብና ቤተ እምነቶችን እንደሚያጠቃ የአለም መንግስታትና የመከላከያ ሰራዊት አመራሮች እየመሰከሩ ነው።

· ሱዳን አርማጭሆን፣ መተማንና ሌሎች ቦታዎችን በወረራ ይዞ፣ ለምን ተብላ ስትጠየቅ፣ የሱዳኑ ጀኔራል ዶ/ር አብይ ፈቅዶልን ነው ማለታቸው እንደተጠበቀ ሁኖ፤ ጠቅላይ ሚኒስተሩ ወረራውን አላወገዙም፣ ለዓለም መንግስታትም ድርጊቱን አላሳወቁም። ይህም የተበላሸ ዲፕሎማሲን፣ የሀገር ዘላቂ ጥቅሞችን አሳልፎ መስጠትን፣ ባጠቃላይ ሀገርን ዋጋ የሚያስከፍል የክህደት ተግባር ነው።

· ሰላማዊ ሰልፍን በተመለከተ መንግስት ለተቃዋሚ ፓርቲዎች በተደጋጋሚ ከልክሎ በአንፃሩ ራሱ ገዢው ፓርቲ ወይም የሚቆጣጠረው መንግስት ሲፈልግ ግን ሰልፍ ጠርቶ ሰላማዊ ታጋዮችን ያወግዝበታል።

በዶ/ር አብይ የሚመራው ብልፅግና ፓርቲ ወጥነት ስለሚጎድለው ህዝብ በመንግስት ቃል ለመተማመን እንዲቸገር ተደርጓል። “ኢትዮጵያ አትፈርስም” ብሎ ደጋግሞ በመናገር ብቻ አገርን ከማፍረስ ማዳን አይቻልም። ምክያቱም የአገራችን የህልውና መሰረት ተናግቶ፣ የሰብዓዊ መብት ጥሰት እየተፈፀመ፣ ህዝብን በጅምላ የማጥፋት ጥቃት እየተፈፀመ፣ የገባ የኤርትራና የሱዳን ወታደር ድንበር ጥሶ በአገርና በህዝብ ላይ ጥቃት እያደረሰ እርምጃ ሳይወሰድ ኢትዮጵያ አትፈርስም ማለት ከንቱ ድለላ ነው።

ዐማራው ኢትዮጵያዊነትን ከፍ በማድረጉና በማክበሩ በጠላትነት ተፈርጆ መስዋእትነት ከፍሎባታል። በኢትዮጵያን ታሪካዊ ጠላቶች እሳቤና የስሁት ትርክቶች መሰረተ ተደርጎ የተሰራውና በሀገር ላይ የተጫነው የትህነግ / ኦነግ የአፓርታይድ ሥርአት አራማጅ ተረኛ ጁንታዎች አመራር ሰጪነት ዐማራው በጭካኔ በብዙ አካባቢዎች በስፋት መጨፍጨፉ ቀጥላል። ህዝብ ያለይሉኝታ የሚዘረፍበት የጅብ ዘመን ውስጥ ተዘፍቀናል። ጠቅላይ ሚኒስትሩ ኢትዮጵያዊነት እየሰበኩ ህዝብን ሊያማልሉ ቢሞክሩም፣ ባለፉት ሦስት አመታት በተግባር እየሆነ ያለውና ገሀዱ እውነት ግን የሀገር ህልውናን አደጋ ላይ የጣሉ ውድቅ መሪ መሆናቸውን ነው። የዐማራውን ጠንካራ ኢትዮጵያዊነት በጠላትነት ፈርጆ ህልውናውንና ማንነቱን ሳያከብሩ፣ ሀገር ለማፍረስ ቀንና ሌሊት የሚሰሩት ተረኞች ዐማራውን ደጋግሞ መካድ ተግባራዊ ልምዳቸው ሆኗል። **ኢትዮጵያዊነትን ከፍ ማድረጉንና ማክበሩን በድክመት በመውሰድ፣ “ለኢትዮጵያ እንደሀገር መቀጠል” በሚል ባዶ ድለላ በወልቃይት፣ ጠገዴ፣ ጠልምትና እራያ በመስዋእትነቱ ያስከበረውን ህልውናውንና ማንነቱን ለመቀማት የሚደረገው የኦሮሚማ ተረኞች ጥረት፣ በግልጽ ከነገሩን “በማሳመን ወይም ግራ ማጋባት” ስልታቸው የተለየ ስላልሆነ ዐማራውን መፈታተናቸው የማይቀረውን ውድቀታቸውን እንደሚያፈጥነው ሊያውቁት ይገባል። በአማራው ህልውና ላይ ተረማምደው ስግብግብና አረመኔያዊ ህልማቸውን እውን ለማድረግ መሞከር ከታሪክና በቅርብ ካየነው የትግራይ ወያኔ ወድቀት አለመማር ነው።**

ለዐማራ የማንነትና የህልውና ጥያቄ ግብ መሰረታዊ የሆነ የስርዓት ለውጥ በኢትዮጵያ ማምጣት ወሳኝ ነው። ህዝቡ የእኔ ብሎ በሚመርጠው የለውጥ ጎዳና መጓዝ ይኖርበታል። የኢትዮጵያ መንግስት የምንለው በሕዝቡ እጅ እስኪገባ ድረስ የሽግግር መንግስት እውን ማድረግ ወሳኝ ነው። ለዚህ ሂደት ዐማራው ከሌሎች አገር ወዳድ ወገኖቹ ጋር በመሆን የራሱን አሻራ ለመጣል አዲስ የለውጥ ኃይል ማዋቀርና ማዋሃድ አለበት ። ለዚህ ግብ ለመብቃት ዋናው ማያያዣው ቁልፍ የዐማራ የቆረጠ ትግል ነው። የኢትዮጵያ መዳኛ የዐማራ መደራጀትና ከሌሎች አገር ወዳድ ወገኖቹ ጋር በመሆን መደራጀቱና ጠንካራ ኃይል ሆኖ መውጣት ብቻ ነው። ***ዐማራው ለዘረኞች ሰለባ መሆኑ እንዲቆም ከተፈለገ፣ እንዲሁም ዐማራው የተጋረጠበትን የህልውና መጥፋት ለመመከት የአባቶቹ አገር ባለቤትነትና በአገሩ ሰርቶ ለመኖር ያደረጉትን ገድል በመንፈሱ ሰንቆ በአንድነት መነሳት ይኖርበታል።***

አንድ ዐማራ ለሁሉም ዐማራ፤ ሁሉም ዐማራ ለዐንድ ዐማራ!

ፈለገ አሥራት የትውልዳችን ቃል ኪዳን ነው!